# ዕቃዎች በጊዜያዊነት አገር ውስጥ የሚገቡበትና በአገር ውስጥ ስለሚቀሩበት ሁኔታ እና የቀረጥና ታክስ ክፍያ አፈፃፀም የወጣውን መመሪያ ቁጥር 28/2002 ለማሻሻል የወጣ መመሪያ

ዕቃዎች በጊዜያዊነት አገር ውስጥ የሚገቡበትና በአገር ውስጥ ስለሚቀሩበት ሁኔታ እና የቀረጥና ታክስ ክፍያ አፈፃፀም የወጣውን መመሪያ ቁጥር 28/2002 ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

መመሪያው እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ዕቃዎች በጊዜያዊነት አገር ውስጥ የሚገቡበትና በአገር ውስጥ ስለሚቀሩበት ሁኔታ እና የቀረጥና ታክስ ክፍያ አፈፃፀም የወጣውን መመሪያ ለማሻሻል የወጣ መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ማሻሻያ

1. የመመሪያ አንቀጽ 8(3) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 8(3) ተተክቷል፡፡

    3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም በዕቃው ላይ የደረሰው ጉዳት ዕቃውን ሙሉ በሙሉ ከአገልግሎት ውጪ ያደረገው እንደሆነ ጉዳቱ ከመድረሱ በፊት ባለው የእርጅና ቅናሽ ላይ በገቢ ግብር አዋጅ በተደነገገው የእርጅና ቅናሽ ስሌት መሠረት ቀረጥና ታክስ ይከፈላል፡፡

2. ከመመሪያው አንቀጽ 8(3) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (4) ተጨምሯል፡፡

    4. በጊዜያዊነት ወደአገር ውስጥ ገብተው የቆይታ ጊዜያቸውን አጠናቀው የሚመለሱ ዕቃዎች የእርጅና ቅናሽ ላይ ቀረጥና ታክስ የሚከፈለው በገቢ ግብር አዋጅ በተደነገገው የእርጅና ቅናሽ ስሌት መሠረት ይሆናል፡፡ ሆኖም ለቀረጥና ታክሱ ስሌት በገቢ ግብር አዋጅ ስለጋራ (ፑል) የእርጅና ቅናሽ ስሌት የተደነገገው ተፈፃሚ የሚሆነው በጊዜያዊነት ወደአገር የገቡ ዕቃዎችን በሚመለከት ብቻ ይሆናል፡፡

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን
Ethiopian Revenues and Customs Authority
Records & Documentation

3. <u>ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ</u>

ይህ ማሻሻያ ከግንቦት 17 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ግንቦት 07 ቀን 2007 ዓ.ም

ሱፍያን አህመድ
የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት
ሚኒስትር

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
Ethiopian Revenues and Customs Authority
Records & Documentation No. 2
ኢኮኖሚ ልማት